# ቁጩ አማሮችና የ30ኛው ዓመት በዓላቸው

በወንድሙ መኰንን፣ ሎንደን ኅዳር ፪ሺ፫

ወያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ኗሪውን ወገናችንን ሙሉ በሙሉ እንደተቆጣጠረ ገምቶ ዕብሪት ቢሰማውም፣ ሕዝባችን የወያኔ አስተዳደር ላይ ያላውን ምሬት ያለፍርሀት ከመግለጽ፣ ወደኋላ አላለም። ታዲያ፣ ይኸ ሕዝብ የናቀ የማፊያ መንጋ፣ ውጭ አገር የምንኖረውንም ለመቆጣጠር ባለው ሕልሙ መሠረት፣ በሚኒስተር/ካውንስለር ወይም ያ በሌለበት አገር በአንደኛ ጸሐፊ የበላይነት ወያኔ ኤምባሲ መሠረቱ/ቤዝ ያደረገ በሺ የሚቆጠሩ ለሆዳቸው ያደሩ የሰላዮች ቡድን በየዋና ከተማው አስገብቶ ያሰማራና ሊያጠምደን እንደተዘጋጀ ከዚህ በፊት በአማርኛ "ዘመነ ወያኔ ዘመነ ጨለማ" ርዕስ ጽፌ በኢትዮሜዲያ፣ በኢትዮጵያ.ኦርግ፣ በኢ ኤም ኤፍ፣ በአዲስ ቮይስ ድረገጹጾች መበተኔ ይታወሳል[1]።

## ቁጩ አማሮች

ቁጩ (የውሸት) አማሮች ያልኳቸው እነማን ናቸው? በጠቅላላው ሲታይ ወይ ለሆዳቸው ሲክለፈለፉ በወያኔ ሸረረት ድር[2] ተጠምደው "ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ነቅናቄ" (ብአዴን) በሚባል የወያኔ የዘር ዘንቢል ውስጥ ታጉረው ያረፉ ሆድ አደር አማሮች፣ አለበለዚያም፣ በምንም ዓይነት አንዲት ጠብታ የአማራ ደም እንኳን በደም ሥራቸው የማትዘዋወር፣ ዳሩ ግን አማራ የሚባለውን 'ዘር' (ያውም ካለ ነው) **ጥምድ** አድርገው የሚጠሉ፣ አማራ የሚባል 'ጎሳ' እንዳይነሳባቸው በፍራቻ ተጠምደው ለመካላከል ብቻ አማራ ነን ብለው ዘንቪሉ ውስጥ እራሳቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የከተቱ አስመሳይ ጆር ጠቢ "ቁጭ በሉ" አማሮች ናቸው። ሀሳቡን ያገኘሁት ከመጀመሪያዎቹ ቁጩ አማሮች፣ አንዱ የነበረ፣ አሁን ራሱን ነጻ ካወጣው፣ ተስፋዬ ገብረአብ ከሚባለው ደራሲ መጽሐፍ፣ "የደራሲው ማስታወሻ" ነው። ተስፋዬ "ጥቁር አማሮች" ይላቸዋል። ጥቁር ቆንጆ ቀለም ነው። ዛሬ የአውሮፓ ወይዛዝርት ለዕራት ሲወጡ፣ ዓይን የሚስብ ጥቁር ቀሚስ ለብሰው ነው፣ የሚሽቀረቀሩት። ፋሽን የተባለ ሁሉ፣ የወንዶች ሱፍ ሙሉ ሱፍ ሳይቀር ጥቁር ይመረጣል። ታዲያ እኔ እነዚህን ጥቁር አማሮች ከማለት በአራዳው አባባል "ቁጩ" ወይም የውሸት አማሮች ብዬአቸዋለሁ። ተስፋዬ ሲያብራራም፣ የእንግሊዝኛውን ቃል ተውሶ ፎርጅድ (forged) አማሮች ብሎአቸዋል[3]። ለነገሩ፣ ጥቁር አማሮች የሚባለውን ስም ያወጣላቸው ተስፋዬ ሳይሆን፣ እራሳቸው ድሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ንቅናቄ ((ኢሕዴን) አባላት በማለት ይጠሩ የነበሩ ከኢሕአፓ ተገንጥለው የወጡ መሆን እንደነበረባቸው እርሱ ፍንጭ ሰጥቶናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቅናቄ ተብለው እንዳይቀጥሉ፣ "ኢትዮጵያ" የምትለዋን ቃል ወያኔ ስለሚጠላና ስላልፈቀደላቸው በዘር እንዲደራጁ አስገድዶአቸው "ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያው ንቅናቄ" (ብአዴን) ብሎ ወያኔያዊ ክርስትና አንስቷቸው፣ "ብዙ ተባዙ አማራን በክሏት" ብሎ ታርጋ ለጥፎባቸው የሰደዳቸው ናቸው። አሁን በውስጣቸው የቀሩትን ወይም ኋላ ላይ የተጨመሩትን ሆዳም አማሮች እንዳሉ ለጊዜው እንተዋቸውና፣ አማራ የሚባል ኃይል በራሱ ተደራጅቶ እንዳያንሠራራ በመፍራት ብቻ በሾርኒ የጠቆሩትን ሀቁ ግን፣ እንኳን አማራነት ስሙም የሚሰቀጥጣቸውን ለአንድ አፍታ፣ ለናሙና ያህል ጥቂቶቹን አንስተን እንያቸው።



ዋነኛው አንዲት የአማራ ደም ጠብታ ሳትገኝበት የወያኔው ብሔረ አማራ መሪ የሆነው የአማራ ባላንጣ ዘረኛ፣ በረከት ስምዖን ነው። በረከት ስምዖን፣ አማራን እንደ ጭራቅ የሚፍራው፣ እንደ እርኩስ የሚጠየፈው ኢትዮጵያው ውስጥ ተወልዶ ያደገ አምቼ ኤርትራዊ ነው። ሌላው ኤርትራዊ አምቼ እዚያ ዘምቢል ውስጥ የተሞጀረው ሕላዊ ዮሴፍ የተባለው ነው። ምናልባት ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ፣ የኤርትራ ድርጅት ፈጥሮ መንቀሳቀስ ስለሚያስነቃ፣ አማሮች የሚባሉ ጉዶች ደግሞ፣ ጉድ እንዳያፈሉባቸው፣ አማራ እንዳያንሰራሩባቸው የአማሮች ድርጅት ተብዬውን ብአዴን ከውስጥ እንዲጠብቁ እራሳቸውን የተከሉ ፊርማቶሪዎች (ቃሉን አውቄ ነው የተጠቀምኩት) መሆን አለባቸው። የበረከትን የአማራ ጥላቻ ለመረዳት ብዙ መዳዝ አይጠበቅብንም። ወያኔ ያደራጀው፣ በራሱ መልክ ጠፍጥፎ የሠራው "የአማራው ድርጅት" መሪ ተብሎ ሲሰየም፣ በረከት ስምዖን ቪ ኦ ኤ የአማርኛው ክፍል በተደጋጋሚ ቃለ መጠይቅ ሊያቀርብለት ሞክሮ "እምቢዮው" ያለ፣ የትግርኛው መርሀ ግብር ላይ ግን ሲለፋደድ የሚውል፣ በተሰባበረ የእንግሊኛው የእንግሊዝኛውን ፕሮግራም የሚያጣብብ፣ የኤርትራን ጥቅም ለማስጠበቅ የቆመ ቁጩ አማራ ነው። ስለዚህ ሰውዬ "አማራነት" ለመገንዘብ ተስፋዬ ገብረአብ፣ አንዳርጋቸው ጽጌን ጠቅሶ፣ በመጽሐፉ ያስነበበን መረጃ ብቻ በቂ ነው። ይኸ ከአረመኔ የባሰ ጨካኝ፣ በጁ የብዙ አማሮችና ኦሮሞዎች ደም ይጨህል። አማራ ነኝ ብሎ እራሱን የሚጠራ፣ ከዚህ የጥላቻ ማሰሮ ጋር አብሮ ከአንድ ማዕድ የሚቆርስ አማራ፣ እንደ የሎንደኑ ያለው ከበደ ዓይነቱ የባሰበት ሆድ አምላኩ መሆን አለበት።



ሌላው ቁጩ አማራ፣ አዲሱ ለገሥ ነው። ኦሮሞነቱን ውስጥ አዋቂው ተስፋዬ ገብረአብ አስነብቦናል። ያስ ደግሞ፣ እራሱን ታምራት ላይኔ ብሎ ሰይሞ አማራ ለመመስል የሞከረው ጉደኛ። ለመሆኑ፣ ትክክለኛ ስሙ ጌታቸው ማሞ ዋቅኬኔ መሆኑን ታውቃላችሁ? ከቁጩ አማራ መሪዎች መሀል፣ ተፈራ ዋልዋ ጊሚራ መሆኑ የታወቀ ነው (ፎቶው የሱ ነው)። በዘር እንደራጅ ከተባለ፣ ተፈራ ድቡብ ገብቶ ወያኔን ያገልግል እንጂ አማራ ውስጥ ምን ዶለው? ታደሰ ጥንቅሹስ? ታደሰ ጥንቅሹ ስሙ ይመር እንጂ ትግሬ ነው። ብአዴን ደግሞ የሕወሀት ሌላው የትግሬ ክንፍ ካልሆነ የጥንቅሹን ልጅ እዚያ ውስጥ ምን ሸነቀረው? በዘር እንደራጅ ካሉ ትግሬው አማሮች መሀል ምን ይፈይዳል? ነገሩ ተነገሮ አያልቅም። እንዲያው የዲ ኤን ኤ ምርመራ ቢደረግ፣ ብአዴን የአማራ ድርጅት ሆኖ ከመገኘት ይልቅ የወያኔና የሻዕቢያ የጋራ ድርጀት ተብሎ መጠራት ይቀለዋል። የሌሎቹም ወያኔ የጠፍጠፋቸው የጎሳ አስመሳይ ድርጅቶችም ዕጣ ፈንታቸው ያው ነው። ወያኔ ነው ሌላ ገሳ ደርቦ የሚነዳቸው። ብአዴን አማራ ለመሆን ከቶም አንዳች የአማራነት ንጥረ ነገር አይገኝበትም። እነ ተስፋዬ በነበሩበት ጊዜ፣ ከቁጩ አማሮች መሀል፣ አመራር ከያዙት፣ በደም ትንሽ ይጠጋጋል የሚባለው፣ አንድ ጀኔራል ኃይሌ ጥላሁን የሚባል ብቻ ነበር። እሱም ቢሆን ከደቡብ ተገኝቶ ደብረ ብረሀን ያደገ ነው እንጂ፣ አማራነቱ አጠራጣሪ ነው። ዛሬም ቢሆን ከዚያ የተለወጠ ነገር ሊኖር አይችልም። በቁጩ አማሮች ተመሥርቶ በቁጩ አማሮች እየተመራ ያለ የወያኔ ክንፍ ነው። ኸረ የሆነ ነገር ክንፉን ይስበረው!!!

---

[1] http://wondimumekonnen.blogspot.com/2010/09/blog-post.html
[2] http://wondimumekonnen.blogspot.com/2010/09/blog-post.html
[3] ተስፋዬ ገብረአብ (2002) የደራሲው ማስታውሻ፣ ዋሽንግተን ዲሲ፣ ገጽ 123 – 128

## ወያኔና ገፈፋው

ወያኔ የውጭ ምንዛሪ እጥረት አንቆ ይዞታል። ስግብግብም ስለሆነ፣ ቢሊዮን ዶላር ቢያገኝም መንገብገቡን አያቆማትም። “ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳላ”! ባለሥልጣናቱ ያካበቱት ዩሮ፣ ዶላርና ፓውንድ ውጭ አገር በሚገኙ ባንኮች ተሰውሯል። ካስፈለገ፣ ልረገምና በዚህ ልኮነን። ያ የበዘበዙት የኢትዮጵያ አንጡራ ንበረት መሆኑ ቀርቶ “የግል” ሀብታቸው ስልሆነ ሊነኩት አይፈልጉም። በየአገሩ ዋና ዋና ከተሞች ገንዝብ መንዛሪ ኪዮስክ ከፍተው[4]፣ ለዘመዶቹ/ቿዋ ገንዘብ መላክ የሚፈልግውን/የምትፈልገውን ሁሉ እያጠመዱ፣ ሌላው ላይ መንገድ ዘግተው እነሱ ለብቻቸው (በሞኖፖል) የወጪውን ምንዛሪ ተያይዘውታል። አንድ ጊዜ ይኽ ተደርሶበት፣ በጋዜጣ[5] ወጥቶ፣ የስቶክዌሉ ኪዮሳካቸው የሚዘጋ መስሎን ነበር። አሁን አሁን እንዲያውም ብሶበታል። የዓለም ባንክ በየዓመቱ $3.2 ቢሊዮን ዶላር በዚህ መልክ እንደሚገባ አብስሮናል። ያ ሁሉ የሚገባው ወያኔ ኪስ ውስጥ ብቻ ነው። እነዚያ ገንዘብ የሚመነዝሩ ኪዮስኮች፣ የወያኔ የግል ንብረት ናቸዋ! አገሪቱ አንዲት ሰባራ ሳንቲም ከዚያ አታገኝም። ለም መሬቷንም ሸጠው፣ ብሩ ስለማይበቃቸው፣ አሁን ከዚያችው ከማትነጥፈው ጥገት፣ ከውጭ ኗሪ ኢትዮጵያውያን (Diaspora) በተለያየ ዜዴ ገንዘብ እያሰባሰቡ ነው። አንዱ ዘዴ፣ ኢትዮጵያዊው የውጭ ኗሪ በአገር ባንኮች ውስጥ ጠንካራ ገንዘብ (hard currency) እንዲያስቀምጥ ማባብል ነበር[6]። ሌላው ዘዴ ዘረኝነትን ወደ ውጭ ልከው (ኤክስፖርት አድረገው) ሁለት ወፍ በአንድ ድንጋይ ለመግደል ያደረጉት ሙከራ ነው። ያም ዘዴ፣ የአማራ ልማት ማኅበር (አማራውንም እንደገና ደግሞ ከፋፍሎት፣ የጎንደር ልማት ማኅበር፣ የጎጃም ልማት ማኅበር)፣ የኦሮሞ ልማት ማኅበር፣ የጉራጌ ልማት ማኅበር ወዘተ እያለ በየኤምባሲአቸው ቅጥር ግቢ ለቁጥጥር እንዲያመች፣ ከላይ እንደገልጽኩት፣ በገፍ ከአገር ውስጥ ባስገባቸው የስለላ ባለሟሎች አማካኝነት ሰብስቦ በስለላ ኃልፊው ሊቀመንበርነት ማደራጀት ነው። አንዱ ጥቅም፣ ውጭ ኗሪውን ኢትዮጵያዊ ለመከፋፍል ያቀዱት ሴይጣናዊ ክፍፍላቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል፣ “ክልልህን አደራጅ በማለት” ገንዘብ ሲያዋጣ ጠንካራውን ዶላር፣ ዩሮ ወይም ፓውንድ ለመንጠቅ ነው። ሎንደን ውስጥ ይኽን ሙከራ ሜይ 29[7] ላይ አድረገው ነበር። በጊዜው “ወያኔ አማራን ሲያጠፋ እንጂ ሲያለማ አላየንምና አትንቀሳቀስ” ብለን ብንጮኽም ሆዳቸውን ብቻ ያዩት ቁጩ አማሮች ተሰብስበው በልተው፣ ጠጥተው፣ ሰክረው ተሳክረው ሕሊናቸውን ስተው፣ ስብዕናቸውን ሸጠው £13 000 እንዳስረከቡ፣ የወያኔ ድረ ገጽ[8] አስነብቦናል። ወያኔ፣ “መሬት ተመርታችሁ፣ ቤት ሥሩ” ብሎ አታሎ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ገንዘብ እንደነጠቀ በቅርብ የምናውቀው ታሪክ ነው። “አገር ቤት ንዋይ አፍስሱ” እያለ አስገብቶ ኢኮኖሚያዊ ድርጅት ሲያቋቁሙ የሚረዳ መስሎ አብሮአቸው እንገፍ-እንገፍ እያለ ያ ድርጅቱ ተገንብቶ ሲያልቅ ተነጥቀው ባዶ እጃቸውን ወደመጡበት የተመለሱና “ዋይ ዋይ!” የሚሉ ኢጋጥመውናል። ታዲያ ይኽ አስቀያሚ ዕድል የገጠማቸው ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ፣ ከወያኔ ባለሥልጣናት ጋር ተሻርከው ቢዝነስ ሊሠሩ ያቀዱ ፈረንጆችም[9] ጭምር ነበር። አንዳንዶቹን ድርጅቱን ባይነጠቁባቸውም የአቋቋመውትን እዚያው ተተው ወደ መጡበት የተመለሱትን ዜጎች ለመቆጣጠር ወያኔ አንድ አዋጅ አስተላልፏል። እሱም፣ እያንዳንዱ አገር ውስጥ ቤት የሠራም ይሁን፣ ድርጅት ያቋቋመ፣ ኤምባሲ ድረስ እየሄድ የጣት አሻራ እንዲሰጥ ጥብቅ ትዕዛዝ ተመርቶበታል። ቀልዴን እንዳይመስላችሁ። የምሬን ነው። የኤምባሰው ድረ ገጽ ድረስ በመሄድ ማንበብ ትችላላችሁ[10]። በነገራችን ላይ እያንዳንዱ በቁጥር ከግረጌው ያስመልከትኩት በሀቅ የተደገፈ መረጃ ነውና ከማንበብ አትቦዝኑ። አሁንም እንግዲህ የወያኔ ሽረሪት ድሯን አድርታ ነቅታ ትጠብቃለሽ። የሚገባላት ካለ፣ “ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽም አይከፋሽ” ከማለት በስተቀር፣ ሌላ የምንለው አይኖርም።

ወያኔ የልብ ልብ ተሰምቶታል። የአገራችንን ሕዝብ ሕይወት ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮታል። አሁን አንደኛውን እኛን ለመቆጣጠር ፊቱን ወደ ዳያስፖራው አቅንቷል። ጥሩው ምሳሌ የሚሆነው ባለፈው ሰሞን ዋሽንገትን ዲስ 50 የሚሆኑ የወያኔ ደጋፊዎች በሆዳደሩ ስሎሞን ተካልኝ “ቅንድቡ ያማረ[11]” ዜማ እየታጀቡ ያደረጉት የድጋፍ ሰልፍ ዋናው መረጃችን ነው። ሰውንም እያታለሉ፣ “ኑ፣ ግብጽ አባይን ልተወስድብን ነውና ተቃውመን፣ ለአገራችን እንሰለፍ” በማለት፣ ያልጠረጠረውን ለማሰለፍ ሞክረዋል! ድሮ ተሸማቅቀው፣ አንገት ደፍተው እንዳልሄዱ ዛሬ አንገታቸውን ቀና ማድረግ ደጃችን ደርሰዋል። ጎብዝ! ተጠቅተናል! ተደፍረናል!

## የቁጩ አማሮች 30ኛው ዓመት

ይኽንን ጽሑፍ የጀመርኩት ብአዴን በሚባለው ቁጩ አማሮች በተሰገሰጉብት የወያኔ ዘንቢል ነበር። ታዲያ ያ የዘረኞች ዘንቢል፣ 30ኛ ዓመት በዓሉን በኢትዮጵያ ሳይሆን በሎንደን ሊያከብር መነሳቱን በወያኔ እምባሲ ድረ ገጽ ተነገረን[12]። የሚገርመው፣ አንድም አማራ የተባለ ሌላ ድረ ገጽ ነገረ ሥራቸውን ሳያስተጋባው “የምጣዱ እያለ የዕንቅቡ ተንጣጣ” ሆኖባቸው ማስታወቂያውን ከድምጹ በላይ ማጭህ የጀመሩት የወያኔ ድረ ገጾች ሁነው ተገኙ[13]። ወቸ ጉድ!!! ዕውነትም ቁጩ አማሮች!

ሎንደን ውስጥ አማራ ሳይሆኑ ለማስመሰል አማራ የሆኑ እና፣ አማራ ሁነው ለሆዳቸው ሲሉ ብቻ እናታቸው የሚሸጡ እንደ እነ ያለው ከበደ (ጎንደር አሰዳቢ!) ያሉ ቁጩ አማሮች ተሰግስገውባታል። ለነገሩስ እነ ሥዩም በረደድስ እነሙሉጌታ አሥራተን የመሳሰሉትን ቁጩ ሆድ አደር አማሮች ከሎንደን አልነበር የመለመሉት!

---

[4] http://www.ethiomedia.com/carepress/meles_zenawi_money_laundering.html
[5] http://in.reuters.com/article/idINIndia-46285220100218
[6] http://wondimumekonnen.blogspot.com/2010/05/blog-post_27.html
[7] http://wondimumekonnen.blogspot.com/2010/05/blog-post_29.html
[8] http://www.ethioembassy.org.uk/community/Community.htm
[9] http://www.ethiopianreview.com/content/2989
[10] http://www.ethioembassy.org.uk/community/news_archive/announcement_06_10013.pdf
[11] http://www.ethiotube.net/video/10237/Woyane-Supporters-marching-in-Washington-DC
[12] http://www.ethioembassy.org.uk/image/andm_ad.jpg
[13] http://tigraionline.com/andm_anniversary.html



አሁንም፣ ኖቨምበር 27 ቀን 2010 (በፍረንጆች) ወይም ኅዳር ፲፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም (በኛ) ድብልቅልቁ የወጣለት የቁጩ አማሮችን ብአዴን 30ኛ ዓመት ክብረ በዓል ለማክበር ድፋ ቀና፣ ሽር ጉድ እያሉ ነው። ዕውነተኛ አማሮች በዘር አልተደራጁም። ኢትዮጵያዊነታቸው ስለሚበልጥባቸው አብዛኞቹ ዘረኝነትን አውግዘው በኢትዮጵያዊነት ከሌሎቹ ጋር ቀጥ ብለው ያለማወላወል ቁመዋል። በዘርም የተደራጀ አማራ ቢኖር ከወያኔ ጋር አሸሻ ገዳሜ ለማለት በወያኔ ኤምባሲ ቅጥር ግቢ ውስጥ አይሰበሰብም። ስለዚህ ልክ ኢትዮጵያ እንደሚደረገው ከአማራ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው ቁጩ አማሮች በአማራ ስም ተሰብስበው ሲድልቁ ውለው በአሰረሽ ምቺው ሲምነሸነሹ ሊያድሩ ነው። ይኸ አማራነት ሊከበርበት የተዘጋጀ ድግስ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያዊነት ሊዋረደበት፣ የወያኔ ዘረኝነት ሊነግስበት የተዘጋጀ የቁጩ አማሮች ግብር 30ኛ ዓመት ዝክር ነው። ድግሱ የዘረኞች፣ የአስመሳይ አማሮች እንጂ የአማራ በዓል እንዳልሆነ፣ እነሱም ያውቁታል፣ አማራውም ያውቀዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የወያኔን የንብ ምልክት ሌላ ስም እየሰጠው በድፍረት ምሬቱን ሲግልጽ፣ ምን ዓይነት አማራ ነው ውርደትን ለማክበር ወያኔ ግቢ የሚሰበሰበው? እነዚህ እንደ ተምች አገሪቱን የወረሩ፣ ግጠዋት ያለሥጋ በአጥንት ያስቀሯት፣ መሬቷን ለባዕድ በረካሽ የቸበቸቡ፣ የወጣላቸው የማፊይ መንጋ ናቸው። እንዴት አገሩን፣ ወገኑን የሚወድ ሰው ከነዚህ ማፊያዎች ጋር ግንባር ይፈጥራል!

ኢትዮያውያን ስደተኞች፣ እኛም ዕለቱን እንዘከረዋልን። እነሱ ከውስጥ፣ እኛ ከውጪ! የፎቶና የተንቀሳቃሽ ፊልሞች ማንሻ ካሜራዎቻችንን አንግበን በዕለቱ የቀድሞ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በነበረው 17 ፕሪንሰስ ጌት ላይ እንገኛለን። በአካባብውም በብዛት በመገኘት እንደተለመደው ጩኸታችንን እናስተጋባለን። ሆድ አድሮቹንና አማራ ሳይሆኑ በአማራ ስም የሚነግዱትን ቁጩ አማሮችን ድምጻችንን ከፍ አድረገን እናወግዛቸዋለን። ከዚህ በፊት በዚያችው ቦታ ኢትዮጵያውያን በንዴትና በምሬት ወጥተን ለብዙ ሳዓታት የናይትስ ብሪድጂን መንገድ ዘግተን ማንነታችንን አሳይተን ነበር። ያንን የማንደግመበት ምክኒያት አይኖርም። በቀኝና በግራ የሚገኙት የሌሎች አገሮች ኤምባሲዎችም እንደቀድሞው መረበሻቸው አይቀሬ ነውና እናዝናለን። እንግዲህ ምን ይደረግ! ከአጋም የተጠጋ ቁልቋልስ ሲያልቅስ አይደል የሚኖረው፣ ከነዘይቤው!

ለንደን ለሚኖር ስደተኛ ኢትዮጵያው መልዕክታችን ግልጽ ነው። ግብዣው ድርሶህ ከሆነ፣ የወገንህን ሥጋ እንድትበላ፣ የወገንህን ደም እንድትጠጣ ሊያረክሱህ ነውና ተጠንቀቅ! ከነዚህ ነጂሶች እራስህን ጠብቅ። በደጃፋቸውም ዝር አትበል። አትነካካ!

# <u>ዶቼ ቬሌን ምን ነካው?</u>

ሌላው መልዕክቴ ዶቼ ቬሌ ለሚባለውን የጀርመን ሬዲዮ የአማርኛ አገልግሎት ሪፖርተር ሆናችሁ ለምታገለግሉ ወንድሞችና እህቶች ነው። ዶቼ ቬሌ አገር ቤት እንዳይሰማ የወያኔ መንግሥት አንቆ እንዳፈነው ልነግራችሁ አልደፍርም? ታውቁታላችኋ! ወያኔ ጸረ ነጻ ፕሬስ ነው። ነጻ መረጃ ለሕዝቡ እንዳይዳረስ፣ አገር ቤት ነጻ ጋዜጣ እንዳይኖር የወያኔ አፋኝ አምባገነን ስንቱን አሥሮ ስንቱን እንዳሳደደ እንዳላጣችሁ አውቃለሁ። ታዲያ ለእንዲህ ዓይነቱ አውሬ አምባገነን ፕሮፓጋንዳውን እንዲያናፋብን መድረክ መስጠታችሁ ማንን ለማስደሰት ወይም የማንን አንጀት ልታሳርሩ ነበር? ይኸ ሮሮዬ የሐሙስ የኖቨምበር 11 ቀን 2010 ዓ ም፣ በሐና ደሚሴ ተቀናብሮ፣ ወያኔ እምባሲ ውስጥ ስለተዘጋጀው የፊልም ዝግጅት ያቀረባችሁ ፕሮግራም ነው። ስለተደረገው ዝግጀት “ሪፖርት ለማድረግ ሙያዊ ገዴታችን ነው” ብትሉንም፣ አልፋችሁ ተርፋችሁ፣ ዝግጅቱን የማይመለከት፣ አንድ ኢትዮጵያዊ አገር ቤት ገብቶ ንዋይ ለማፍሰስ ቢፈልግ የሚደረግለትን እንክብካቤ መጠየቃችሁ፣ ግርሞናል። እናንተም ገብታችሁ ንዋይ ልታፈሱለት ነው? የወያኔው አምባሳደርማ የጠነባውን ፖለቲካ ሊናኝ ዕድል አገኘ። “ክቡር አምባሳደር” እያላችሁ በማቆላጳስ የሰጣችሁትን ዕድል ተጠቅሞ፣ የወያኔ ፕሮፖጋንዳውን ተፋብን። እንደድሮአችሁማ ብትሆኑ፣ ስለሰው ልጅ መብት መገፈፍ፣ ስለነጻው ፕሬስ፣ አፋጣችሁ ትጠይቁት ነበር እንጂ ስለሌለው ልማት፣ ስለባዶ ዕደግቱ ወሬ እንዲፈንጭብን አትጠይቁም ነበር። ምን ነካችሁ? ከዚህ በፊት የሙያ ሥራችሁን እንከን በሌለው አኳኋን ተወጥታችኋል። ለተገፉት የሙያ ባልደረቦቻችሁም ድጋፍ አሳይታችሁአል። በዚህ የተነሳ ነበር ሪፓርተሮቻችሁ ወደ ወያኔው እምባሲ ቅጥር ግቢ እንዳይገቡ የተከለከሉት። ወያኔ የክፋት ጠባዩን ሳይቀይር፣ ምነው እናንተ ተቀየራችሁ? የወገናችሁን አፍ የዘጋውን ቡድን በሬዲዮአችሁ ፕሮፓጋንዳውን እንዲለቀው ዕድል ስትሰጡት ሰሞኑን ሰምተን እንዳዘንባችሁ ይታወቅልን። ምናልባት መንግሥት ስለሚያስተዳድራችሁ ተገዳችሁ ነው ወይስ በገዛ ፈቃዳችሁ ነው ያንን ያደረጋችሁት[14]? እንግዲህ ኖቬምበር 27 ቀን እኛ ወንደሞቻችሁና እህቶቻችሁ ከውጭ ስንጮኽ የናንተ ሪፖርተር ወደውስጥ ገብቶ/ገብታ የቁጩ አማሮችን ደስታና ፈንጠዚያ ተካፍሎ/ተካፍላ፣ ተደስቶበት/ተደስታበት እርካታውን/እርካታዋን ቢያስተጋባ/ብትስተጋባ የኢትዮጵያ ሕዝብ እሪ እንደሚልባችሁ ከወዲሁ ዕውቁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ እጅ እጅ የሚለውን የሌለ ልማት፣ ዕድገት ሲያናፋ በተራበ ሆዱ ላለመስማት ቴለቪዥኑን ዘግቶ እናንተን እና የአሜሪካንን ሬዲዮ ለመስማት በተለያየ ዘዴና ተክኖሎጂ ሬዲዮውን ሲኮረኩር ይውላል። እባካችሁን ለናንተ ሲል ጊዜና ገንሰቡን የሚሰዋውን ወገን የወያኔን ቦይ ሆናችሁ የማይፈልገውን የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ማስተላለፊያ አሸንዳ፣ እንዳትሆነበት፣ ሎንደን የምንገኝ የዕለቱን ተቃውሞ የምንዘጋጅ ወንድሞችና እህቶቻችሁ አደራ እንላችሁአለን።

[14] http://www.youtube.com/watch?v=pMAuxKyx49U&feature=player_embedded

# የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ

ይኸንን ጽሑፍ የማንበብ ዕድል ያጋጠማችሁ፣ ወይም አፊሴላዊ የሆነ የጥሪ ማስታወቂያ በድረ ገጾችም ይሆን ወይም በቅርቡ በሚወጡት በበራሪ ወረቀቶች የሚደርሳችሁ፣ ቀጠሮአችሁ ኖቨምበር 27 ቀን 2010 ዓ ም (27 November 2010)፣ 17 ፕሪንሰስ ጌት (17 Princes Gate) ደጃፍ ላይ ይሁን። መከፋፈላችን አስጠቅቶናልና፣ ኑ አብረን እንከላከል። ከአሁኑ አጀንዳችሁ ላይ ዕለቷን መዝግቧት። ይኸ ስለ አማራ ጉዳይ አይደልም። ዛሬ የአማራን 30ኛ ዓመት አክብራለሁ ብሎ ተነስቷል። ከትንሽ ቀናት በኋላ ደግሞ፣ የኦሕዴድን 30ኛ ዓመት አከብራለሁ ብሎ ቁጩ ኦሮሞውችን ሊሰብሰብና ዳንኪራ ሊረግጥብን ነው። እኛ አጭበርባሪዎችን ለመጋፈጥ፣ ኢትዮጵያዊነትን ለማስከበር ቆርጠን ተነስተናል። 17 ፕሪንሰስ ጌት የምትመጡት ወያኔ ያዘጋጀላችሁን መርዝ ልትቀበሉ ሳይሆን፣ ከወገን ጋር ልትጋፈጡ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያውያንን ክብር ለመታደግ መሆን አለበት። ወደ ወያኔ ግባዣ ስትመጡ፣ እንደከዚህ በፊቱ ፎቶ አንስተናችሁ፣ “ወያኔ! ወያኔ!” የሚል ታፔላ ግንባራችሁ ላይ ለጥፈንባችሁ በየድረ ገጾች ምስሎቻችሁን ከማውጣት ያድናችሁ። ያ ብቻ አይደለም። ያን ቀን የምናነሳቸውን ተንቀሳቃሽ ስዕሎች አንዳሉ ወደ አገር ቤት የምናስገባና፣ የምንበትን መሆኑን ከአሁን ዕወቁ። ወያኔ ፊት ለፊት በመጋፈጥ በየቀኑ መስዋዕትነት የሚከፍሉ ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ ያንን ሲያዩ የሚስማቸውን መሸማቃቅና ስለእናንት ማፍርን አስተውሉት። እንደዚያ ከመሆን ያድናችሁ። አንደበት ላጣ ሕዝብ አንደበት ልትሆኑለት ያብቃችሁ። በዕለቱ ተገኝታችሁ ቁጩ አማሮችን እንድታሳፍሩ በዚህ አጋጣሚ በራሴና በጓደኞቼ ስም ወንድማዊ ግብዣዬን ከወዲሁ አስተላልፋለሁ። ለዚያን ቀን ሰው ይበለን። አሜን በሉ! አሜን!